## የትምህርት ቤቶች አጠቃላይ እቅድ

*እያንዳንዱ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት የትምህርት ቤት ደህንነት ቡድን አለው። ይህ ቡድን የትምህርት ቤቱን ሥነ ልቦናዊና አካላዊ ደህንነት፣  እንደዚሁም እንደአስፈላጊነቱ አደጋን የመቋቋምና መልሶ ግንባታን የማካሄድ ሥራዎችን በመከታተል ይሰራል። በአሜሪካን አገር-አቀፍ ትምህርት ቢሮ (2004) የተሰጠው የድስትሪክቱና የትምህርት ቤት ደህንነት እቅድ ዋናዎቹ ፈርጆች ከታች* በሦስት ማእዘን *የተቀመጠውን ቀጣይ የድስትሪክቱ አካላዊና ሥነ ልቦናዊ የደህንነት* ጥረቶችን ያሳያል።




**የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት**
**ደህንነታቸው የተጠበቁ ትምህርት ቤቶች አጠቃላይ እቅድ**

*የአደጋ (የቀውስ) ጊዜ ዝግጁነት እቅድ ተግባራዊ መረጃ፤ የትምህርት ቤቶችና ማህበረሰቦች መመሪያ መሪ ሃሳብ የድስትሪክቱን ትምህርት ቤቶች የደህንነት እቅድ የሚመሩ አራት አጠቃላይ የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት ደረጃዎችን ይገልጻል።*

### 1. ማቃለል/መከላከል

*የመከላከል እርምጃዎች የሚወሰዱት የሚከተሉትን ለማረጋገጥ ነው፤*

- *በደል፣ ጭቆናና ማስፈራራትን ለመከላከል ሁሉም ማህበረሰቦች ተገናኝተው በጋራ ይሰራሉ።*
- *ትምህርት ቤት፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ ጠቃሚ እሴቶችን በጋራ ይገነባሉ።*
- *የምላሽ ውሳኔ የሚሰጠው በመረጃ ላይ በመሞርኮዝ ነው።*
- *ከተማሪዎች፣ ከሰራተኞችና ከወላጆች የሚጠበቁ ጉዳዮች በግልጽ ይነገራቸዋል።*
- *የማህበራዊ-* የሥነ ልቦናዊ *-የሥነ ምግባራዊ ክህሎቶች ትምህርቶች ይሰጣሉ።*
- *አደጋን የማቃለል ጥረቶች አደገኛ የአከባቢ ሁኔታዎችን በመገምገም ሥጋት መቀነሱን ያረጋግጣል።*

### 2. ዝግጁነት/እቅድ

*ዝግጁነት ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ አስፈላጊውን ውጤታማ የሆነ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችላቸውን የትምህርት ቤቶች እቅዶች ያጠቃልላል። ይህም አስቸጋሪ ጸባይ ላላቸው ልጆች/ወጣቶች ውጤታማ ድጋፍ/እርዳታ ለማድረግ ማቀድንና የልጆች/የወጣቶች የሁከት ስነምግባር የመጀመሪያ ምልክቶችን በተመለከተ አስፈላጊውን እርዳታ እንዲያደርጉላቸው ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎችና ለወላጆች ስልጠና መስጠትን ያካትታል።*

### 3. ጣልቃ-ገብ ምላሽ/እርዳታ

*ድስትሪክቱና ትምህርት ቤቶቹ ለአደገኛ ሁኔታዎች እና/ወይም የተለያዩ ሥጋት ላለባቸው ወይም አደገኛ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ላሉ ልጆች አስፈላጊውን እርዳታ ለማድረግ የሚያስችላቸውን የምላሽ/የእርዳታ ሥርዓቶች አሏቸው። ጣልቃ-ገብ ድጋፎች የተዘጋጁት ከአስቸጋሪ ጸባይ መቆጠብ ላልቻሉና ይህንን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ውስጥ አስፈላጊውን ምላሽ መስጠት ላልቻሉ ተማሪዎች ነው። ይህም የድስትሪክቱ የአደጋ ጊዜ የግምገማ ሂደት ቡድን፣ እንደዚሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የችግር ፈቺ ሂደትን መጠቀምን ያካትታል።*

### 4. የቀውስ ጊዜ ምላሽ/ገገምታ (ማገገም)

*ገገምታ በቀውስ ጊዜና ከዚያም በኃላ ለተማሪዎችና ለሰራተኞች ደህንነትና ማገገም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ የሚወስደውን አግባብ ያላቸውን እርምጃዎች ያካትታል። ዓላማው ትምህርት ቤቱ ደህንነቱ የተጠበቀና ለመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንዲችል፣ እንደዚሁም እንደተለመደው የመማር ማስተማር ሥራውን ማከናወን እንዲችል ማድረግ ነው።*